# ኒያላ ኢንሹራንስ አ.ማ.

## የጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ

### ለኒያላ ኢንሹራንስ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች በሙሉ

የኒያላ ኢንሹራንስ አ.ማ. የባለአክሲዮኖች 29ኛ ዓመታዊ መደበኛ እና 22ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔዎች ቅዳሜ ህዳር 1 ቀን 2016 ዓ.ም. ከጥዋቱ 2:30 ሰዓት ጀምሮ በሸራተን አዲስ አዋሽ የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ይካሄዳሉ፡፡ ስለሆነም የኩባንያው ባለአክሲዮኖች በሙሉ በተጠቀሰው ቀንና ቦታ በሰዓቱ እንድትገኙለት የኩባንያው የዲሬክተሮች ቦርድ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 366(1)፣367(2)፣370፣371(1) እና 393 መሠረት ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

- የኩባንያዉ የንግድ ዘርፍ ------------- ኢንሹራንስ
- የኩባንያዉ የተከፈለ ካፒታል -------- ብር 830,000,000.00
- የኩባንያዉ የንግድ ምዝገባ ቁጥር --- KK/AA/3/0009174/2008
- የኩባንያዉ ዋና መ/ቤት አድራሻ ----- አ.አ. ቦሌ ክ/ከ ወረዳ 04፣ ቤ.ቁ. 330

### የ29ኛዉ የባለአክሲዮኖች ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች

1.1 የድምጽ ቆጣሪዎችን መሰየም፤

1.2 ምልዓተ-ጉባዔ መሟላቱን ማረጋገጥ፤

1.3 የጉባዔውን አጀንዳ ማጽደቅ፤

1.4 እስከ ስብሰባው ቀን የተካሄዱትን የአክሲዮን ዝውውሮች ማጽደቅና አዳዲስ ባለአክሲዮኖችን መቀበል ፤

1.5 የዲሬክተሮች ቦርድ እ.ኤ.አ. የ2022/23 የሥራ ክንውን ሪፖርት ማድመጥና ተወያይቶ ማጽደቅ፤

1.6 እ.ኤ.አ. የ2022/23 የሥራ ዘመን የውጭ ኦዲተሮችን ሪፖርት ማድመጥና ተወያይቶ ማጽደቅ፤

1.7 እ.ኤ.አ. የ2022/23 የተጣራ ትርፍ አደላደል በዲሬክተሮች ቦርድ በቀረበ የውሳኔ ሐሳብ ላይ ተወያይቶ መወሰን፤ክፍያው የሚፈጸምበትን ቀን መወሰን፤

1.8 እ.ኤ.አ. ለ2023/24 የሥራ ዘመን የውጭ ኦዲተሮችን መሾምና አበላቸውን መወሰን፤

1.9 ለቦርድ አባላት ወርሃዊ አበልና ከተጣራ የትርፍ ድርሻ የሚታሰብ ክፍያን መወሰን፤

1.10 የጉባዔውን ቃለ-ጉባዔ ማጽደቅ

# የ22ኛዉ የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች

2.1 የድምጽ ቆጣሪዎችን መሰየም፤
2.2 ምልዓተ-ጉባዔ መሟላቱን ማረጋገጥ፤
2.3 የጉባዔውን አጀንዳ ማጽደቅ፤
2.4 በ21ኛው አ/ጠ/ጉ ካፒታል ለማሳደግ በተወሰነው መሠረት በዲሬክርተሮች ቦርድ የተሠራውን የአክሲዮን ድልድል መርምሮ ማጽደቅ፤
2.5 ከ21ኛው አ/ጠ/ጉ የካፒታል ጭማሪ ጋር በተያያዘ የኩባንያውን መመሥረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 1፣ 5(1) እና 6(1) ማሻሻል፤
2.6 የኩባንያውን ካፒታል ማሳደግ፤
2.7 የጉባዔውን ቃለ-ጉባዔ ማጽደቅ

**ማሳሰቢያ፡**

1. በስብሰባው ላይ መገኘት ያልቻለ ባለአክሲዮን በስብሰባው ጥሪ ወረቀት አባሪነት በተላከው የውክልና መስጫ ቅጽ ላይ ከጉባዔው ዕለት ቢያንስ ሦስት ቀን አስቀድሞ ወኪል በመሰየም አሊያም በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት የተረጋገጠ ውክልና በመስጠት በወኪሉ አማካኝነት ስብሰባውን መካፈል ይችላል፡፡
2. ውክልና የምትሠጡም ሆነ በጉባዔው ላይ በአካል የምትገኙ ባለአክሲዮኖች ማንነታችሁን የሚገልጽ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውን እና አንድ ኮፒ ይዛችሁ እንድትቀርቡ እንዲሁም በውልና ማስረጃ የተረጋገጠ ህጋዊ ውክልና ይዛችሁ የምትሳተፉ ተወካዮች የራሳችሁን እና የወካያችሁን ማንነት የሚገልጽ የታደሰ መታወቂያ ወረቀት ወይም ፓስፖርት ኮፒ ይዛችሁ እንድትቀርቡ እናሳስባለን፡፡
3. ትውልደ ኢትዮጵያዊ የውጭ ሃገር ዜጋ የሆናችሁ ባለአክሲዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያዊነታችሁን የሚያረጋግጥ የታደሰ መታወቂያ ዋናውን እና አንድ ኮፒ ይዛችሁ መቅረብ ይኖርባችኋል፡፡

**የዲሬክተሮች ቦርድ**
**ኒያላ ኢንሹራንስ አ.ማ.**